በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

ጽዮን ምን ማለት ነው?
የታቦትና የጽላት ልዩነት እንዴት ነው?
ታቦተ ጽዮን ማለት ምን ማለት ነው?

1. ጽዮን ማለት

ጽዮን ማለት አምባ መጠጊያ ማለት ሲሆን በኢየሩሳሌም የአንድ ተራራ መጠርያ ስም ነው። በዚህም ተራራና በአካባቢው ኢያቡሳውያን የተባሉ ይኖሩበት ነበር። በኋላ ንጉሥ ዳዊት እነሱን ተዋግቶ ድል አድርጎ የራሱ ከተማ አደረጋት። 2 ሳሙኤል5፣ 6-10 ከዚህ በኋላ የተቀደሰ የዳዊት ከተማ ተብላ ተሰየመች፣ ተጠራች ።መዝሙር 47፤1-5 ህዝቡም ጽዮናውያን ተብለው ተጠሩ ።
እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው አሠርቱ ቃላት የተጻፉበት ጽላትም በከተማው ስም ታቦተ ጽዮን ተብላ ተጠራች። የጽዮናውያን ታቦት ማለት ነው። በህዝቡ ስም ተጠራች።

2. ታቦትና ጽላት



ታቦትና ጽላት የሚለውን ቃል ልዩነት ልብ አድርገን እንመልከት፤ ታቦት ማለት ማደርያ መቀመጫ ወንበር ወይንም ሳጥን ማለት ማለት ነው ። ጽላት ማለት በታቦቱ ውስጥ የሚቀመጠው የእግዚአብሔር ስመ አምላክ የተጻፈበት ማለት፣ አልፋና ኦሜጋ የተጻፈበት ነው ። ይኸውም ልዑል እግዚአብሔር ለሙሴ በሲና ተራራ ላይ አሠርቱ ቃላትን በእጁ በጽላቱ ጽፎ የሰጠው ነው።

> *እግዚአብሔርም ይህን ቃል ሁሉ እንዲህ ብሎ ተናገረ። ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ። ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት*

*አይሁኑልህ። በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ። አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም፤ በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፤ ለሚወድዱኝ፥ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና። የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና። የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ። ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው፤ አንተ፥ ወንድ ልጅህም፥ ሴት ልጅህም፥ ሎሌህም፥ ገረድህም፥ ከብትህም፥ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ፤ እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፥ ባሕርንም፥ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፎአልና፤ ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታል ቀድሶታልም። አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም። አትግደል። አታመንዝር። አትስረቅ። በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር። የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ። (ኦሪት ዘፀ 20፥1-17)።*

ጽላት ተብሎ የሚጠራው በኋላም ጽላቱን ታስቀመጠበት ታቦት (ማኅደር) እንዲሰራ ስላዘዘው በትእዛዙ መሠረት ታቦቱን ሰርቶ ጽላቱን አሠርቱ ቃላት የተጻፈበትን በውስጡ በማስቀመጥ መንፈሳዊ አገልግሎት ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ተጀመረ ። በሃገራችንም ጽላቱ በታቦቱ ስም፤ ታቦቱ በጽላቱ ስም መጥራት የተለመደ ነው።

*ከግራር እንጨትም ታቦትን ይሥሩ፤ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፥ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል፥ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል ይሁን። በውስጥና በውጭም በጥሩ ወርቅ ለብጠው፤ በእርሱም ላይ በዙሪያው የወርቅ አክሊል አድርግለት። አራት የወርቅ ቀለበቶችም አድርግለት፥ እነርሱንም በአራቱ እግሮቹ ላይ አኑር፤ በአንድ ወገን ሁለት ቀለበቶች፥ በሌላው ወገን ሁለት ቀለበቶች ይሁኑ። መሎጊያዎችንም ከግራር እንጨት ሥራ፥ በወርቅም ለብጣቸው። ለታቦቱ መሸከሚያ በታቦቱ ጐን ባሉት ቀለበቶች መሎጊያዎቹን አግባ። መሎጊያዎቹም በታቦቱ ቀለበቶች ውስጥ ይኑሩ፥ ከቶም አይውጡ። በታቦቱም ውስጥ እኔ የምሰጥህን ምስክር ታስቀምጣለህ። ከጥሩ ወርቅም ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፥ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል የሆነ የስርየት መክደኛ ሥራ። ሁለት ኪሩቤል ከተቀጠቀጠ ወርቅ ሥራ፥ በስርየት መክደኛውም ላይ በሁለት ወገን ታደርጋቸዋለህ። ከስርየት መክደኛውም ጋር አንዱን ኪሩብ በአንድ ወገን፥ ሁለተኛውንም ኪሩብ በሌላው ወገን አድርገህ በአንድ ላይ ትሠራዋለህ። ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ወደ ላይ ይዘረጋሉ፥ የስርየት መክደኛውንም በክንፎቻቸው ይሸፍናሉ፥ ፊታቸውም እርስ በርሱ ይተያያል፤ የኪሩቤልም ፊቶቻቸው ወደ ስርየት መክደኛው ይመለከታሉ። የስርየት መክደኛውንም በታቦቱ ላይ ታደርገዋለህ፤ እኔም የምሰጥህን ምስክር በታቦቱ ውስጥ ታኖረዋለህ። በዚያም ከአንተ ጋር እገናኛለሁ፤ የእስራኤልንም ልጆች ታዝዝ ዘንድ የምሰጥህን ነገር ሁሉ፥ በምስክሩ ታቦት ላይ ባለው በሁለት ኪሩቤል መካከል፥ በስርየት መክደኛውም ላይ ሆኜ እነጋገርሃለሁ። ርዝመቱም ሁለት ክንድ፥ ወርዱም አንድ ክንድ፥ ቁመቱ አንድ ክንድ ተኩል የሆነ ገበታ ከግራር እንጨት ሥራ። በጥሩም*

*ወርቅ ትለብጠዋለህ፤ በዙሪያውም የወርቅ አክሊል አድርግለት፤ በዙሪያውም አንድ ጋት የሚያህል ክፈፍ አድርግለት፤ የወርቅም አክሊል በክፈፉ ዙሪያ አድርግለት። አራትም የወርቅ ቀለበቶች አድርግለት፤ ቀለበቶቹንም አራቱ እግሮቹ ባሉበት በአራቱ ማዕዘኖች አድርግ። ገበታውንም ለመሸከም መሎጊያዎቹ እንዲሰኩባቸው ቀለበቶቹ በክፈፉ አቅራቢያ ይሁኑ። ገበታውን ይሸከሙባቸው ዘንድ መሎጊያዎቹን ከግራር እንጨት ሠርተህ በወርቅ ለብጣቸው። ለማፍሰሻም ይሆኑ ዘንድ ወጭቶችዋን ጭልፋዎችዋንም መቅጃዎችዋንም ጽዋዎችዋንም አድርግ፤ እነርሱንም ከጥሩ ወርቅ አድርጋቸው። በገበታም ላይ የገጽ ኅብስት ሁልጊዜ በፊቴ ታደርጋለህ። መቅረዝንም ከጥሩ ወርቅ አድርግ፤ መቅረዙ ከእግሩና ከአገዳው ጋር በተቀጠቀጠ ሥራ ይደረግ፤ ጽዋዎቹም ጕብጕቦቹም አበቦቹም አንድነት በእርሱ ይደረጉበት። በስተጎኑ ስድስት ቅርንጫፎች ይውጡለት፤ ሦስት የመቅረዙ ቅርንጫፎች በአንድ ወገን፥ ሦስትም የመቅረዙ ቅርንጫፎች በሌላ ወገን ይውጡ። በአንደኛውም ቅርንጫፍ ጕብጕብና አበባ ሦስትም የለውዝ አበባ የሚመስሉትን ጽዋዎች፥ በሁለተኛውም ቅርንጫፍ ጕብጕብና አበባ ሦስትም የለውዝ አበባ የሚመስሉትን ጽዋዎች፤ እንዲሁም ከመቅረዙ ለሚወጡ ለስድስቱ ቅርንጫፎች አድርግ። በመቅረዙም ጕብጕቦቹንና አበቦቹን አራትም የለውዝ አበባ የሚመስሉትን ጽዋዎች አድርግ። ከመቅረዙ ለሚወጡ ለስድስቱ ቅርንጫፎች ከሁለት ቅርንጫፎች በታች አንድ ሆኖ የተሠራ አንድ ጕብጕብ፥ ከሁለትም ቅርንጫፎች በታች አንድ ሆኖ የተሠራ አንድ ጕብጕብ፥ ደግሞ ከሁለት ቅርንጫፎች በታች አንድ ሆኖ የተሠራ አንድ ጕብጕብ ይሁን። ጕብጕቦቹና ቅርንጫፎቹ ሁሉ ከእርሱ ጋር አንድ ይሁኑ፤ ሁሉም አንድ ሆኖ ከተቀረጸ ከጥሩ ወርቅ ይደረግ። ሰባቱንም መብራቶች ሥራ፤ በፊቱ ያበሩ ዘንድ መብራቶቹን ያቀጣጥሉአቸዋል። መኰስተሪያዎችዋን የኵስታሪ ማድረጊያዎችዋንም ከጥሩ ወርቅ አድርግ። መቅረዙም ዕቃውም ሁሉ ከአንድ መክሊት ጥሩ ወርቅ ይሠሩ። በተራራ ላይ እንዳሳየሁህ ምሳሌ እንድትሠራ ተጠንቀቅ። ዘፀ.25፣10-ፍም*

ጽላት ማለት የእግዚአብሔር ስም የተጻፈበት የቃሉ ማደርያ ነው። እግዚአብሔር በጽላቱ እያደረ እስራኤልን ይረዳቸው ነበር። ሕጉን ሲጠብቁ፣ ትእዛዙን ሲያከብሩ ጠላት እንኳ ሲነሳባቸው ታቦተ ጽዮንን ይዘው ስለሚዘምቱ ድል አድርገው አሸንፈው ይመለሱ ነበር። ለምሳሌ አፄ ምኒሊክ ፋሺስት ኢጣሊያን ያሸነፉት ታቦተ ጊዮርጊስን ይዘው ዘምተው ነው። ይህም ከጥንት ሲያያዝ የመጣ ታሪክ ማለት ነው።
ሕጉን ሲጥሱ፣ ትእዛዙን ሲያፈርሱ ረድኤት ይለያቸዋል፤ ለጠላቶቻቸውም አሳልፎ ይሰጣቸው ነበር።

ስለዚህም አንድ ታሪክ እንመልከት። ኤሊ የተባለ ታላቅ ሊቀ ካህናት ነበር፤ እርሱም አፍኒንና ፊንሃስ የሚባሉ ሁለት ልጆች ነበሩት። እነርሱም ከአባታቸው ጋር በቤተ መቅደስ ያገለግሉ ነበር። አባታቸው በእድሜ የገፋ የ98 ዓመት ሽማግሌ ነበር። ሁለቱ ልጆች ለአባታቸው አንታዘዝም ያሉ ነበር፤ ቢመክራቸውም አንሰማም በማለት በሕዝቡ ላይ ልዩ ልዩ በደልን ይፈጽሙ ጀመር። ሕዝቡንም እግዚአብሔርንም አስቀየሙ። እግዚአብሔር ታግሶ ቅጣት ሲያመጣ በሕግ አፍራሾች ላይ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው ሕዝብ ላይ ስለሆነ በእስራኤላውያን ላይ በአካባቢያቸው ያሉትን ሰዎች በጠላትነት አስነሳባቸው። በዚህን ጊዜ ሁለቱ የሊቀ ካህናቱ የኤሊ ልጆች ታቦተ ጽዮንን ይዘው ዘመቱ። ከእግዚአብሔር የታዘዘ ቅጣት ስለነበር በጦርነቱ ላይ ብዙ ሕዝብ አለቀ። ብዙዎችም ተማረኩ። የኤሊ ሁለት ልጆችም በጦርነቱ ላይ ሞቱ። ታቦተ ጽዮንም

ተማረከች። ከጦርነቱ አምልጦ የተመለሰ አንድ ሰው ለኤሊ እስራኤላያን መሸነፋቸውን፣ ሁለቱ ልጆቹ አፍኒንና ፊንሃስ መሞታቸውንና ታቦተ ጽዮን በኤፍላውያን መማርኳን ሲነግረው ኤሊ ደንግጦ ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ወድቆ ወዲያው ሞተ።
ሙሉ ታሪኩን (1 ሳሙኤል 4፡1-18) ይመልከቱ።

ወደ ታቦተ ጽዮን እንመለስና በኅዳር 21 ቀን ያደረገችውን ታላቅ ታምር እንመልከት፤ ምንም እንኳ ኤፍላውያን ማርከው ቢወስዷትም እንዴት አድርጋ እንዳሳፈረቻቸው እንመልከት። ታቦተ ጽዮንን ወስደው ዳጉን ተብሎ ከሚጠራው ቤተ ጣኦታቸው አስገብተው ታቦተ ጽዮንን ከታች ጣኦቱን ከላይ አስቀምጠው በሩን ቆልፈው ሄዱ። በማግስቱ ጠዋት ሄደው ከፍተው ቢመለከቱ ጣኦቱ ወድቆ ተሰባብሮ አገኙት። ኤሎፋላውያን በዚህ ሲናደዱ ሳለ እንደገና ልዩ መቅሰፍትን አወረደችባቸው። ከብታቸው አለቀ፣ ሰብላቸውን ተምች መታው፣ አይጥ በላው። (1 ሳሙኤል 6፡1-3) ታቦተ ጽዮን ልዩ ልዩ ተአምራት በማድረግ 7 ወራት እንደቆየች አስቸኳይ ስብሰባ አድርገው ይህን ሁሉ መአት ያመጣችብን ታቦተ ጽዮን ነች፤ ስለዚህ ካሳ ጭምር አድርገን ወደ አገሯ እንመልስ ብለው ተማከሩ። በምክሩም ከተስማሙ በኋላ ወርቅ በሳጥን አድርገው በሁለት ከብቶች በሰረገላ አስቀምጠው ውደ ሃገሯ መልሰዋታል። የእስራኤል ሕዝብ በደስታ በእልልታ ተቀብሏታል። ታቦተ ጽዮን ወደ ሃገሯ ከተመለሰች በኋላ አሚናዳብ የተባለ አንድ አማኝ ሰው ቤት ለ29 አመታት እንዳኖራት (በ1 ሳሙኤል 7፡2) ተጽፎ እናገኛለን።
ንጉሥ ዳዊት ቤተ መቅደስ ሊሰራላት አስቦ እግዚአብሔር ስላልፈቀደለት ድንኳን አሰርቶ በድንኳን ውስጥ መሥዋዕትና ልዩ ልዩ አገልግሎት ይፈጽም ነበር። ከዚያ የንጉሥ ዳዊት ልጅ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ አሰራላት። ንጉሥ ሰሎሞን ለልጁ ለቀዳማዊ ምኒልክ ስለሰጠው ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ኢትዮጵያ አምጥቶ በአክሱም ትገኛለች። አሁንም አለች። ስለዚህ የአክሱም ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ልደት በፊት ቤተ መቅደስ ሆኖ እንደ ኦሪቱ ስነ ሥርዓት አገልግሎት ይፈጸምበት ነበር። ከክርስቶስ ልደት ወዲህ በሃዲስ ኪዳን ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ተብላ ተሰይማ አሁን ይቀደስባታል፣ ይመሰግንባታል።

3. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጽዮን ማርያም ተብላ ለምን ትጠራለች?

እመቤታችን ታቦተ ጽዮን ተብላ የምትጠራበት ምክንያት አለው። ልብ ብለን ታሪኩን እንመልከት።
ታቦተ ጽዮን የእግዚአብሔር ቃል የአስርቱ ቃላት ማኅደር እንደነበርችና የእግዚአብሔር ቃል በእርሷ ውስጥ አድሮ አማንያንን ትረዳቸው እንደነበር ሁሉ፤ እመቤታችንም ቅድስት ድንግል ማርያም ከሴቶች መካከል ተመርጣ የእግዚአብሔር ቃል የወልድ ማደርያ ስለሆነች፣ ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ዘጠኝ ወር ከሦስት ቀን አርግዛ ስለወለደች ማኅደረ መለኮት (የመለኮት ማደርያ) የእግዚአብሔር ወልድ ማደርያ ስለሆነች ጽዮን ማርያም ተብላ ትጠራለች።
ቃል የተባለ ወልድ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ እንዲህ በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። (ዮሐንስ 1፡1) እንዳለው።

በአጭሩ ታቦተ ጽዮን፣ ማርያም ጽዮን ወይም ጽዮን ማርያም ተብላ የምትጠራበት በዚህ ምክንያት ነው።

እኛም የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች በስሟ በተቀረጸው ታቦትና ጽላት ፊት በመንበሯ ፊት እንሰግዳለን። በአማልጅነቷ እናምናለን። እግዚአብሔርም በእርሷ እያደረ ልመናችንን፣ ስዕለታችንን፣ ሃሳባችንን ይፈጽምልናል። በዘመነ ኦሪት ግዜ በታቦተ ጽዮን ላይ እያደረ የአማንያንን ችግር ያቃልልላቸው ይፈጽምላቸው የነበረው አምላክ ዛሬም በታቦተ ማርያም፣ በታቦተ ጽዮን፣ በታቦተ ጻድቃን፣ በታቦተ መላእክት፣ በታቦተ ሰማእታት በሌሎችም እንዲሁም በራሱ ስም በተሰየመው ታቦት ላይ እያደር ጸሎታችንን፣ ልመናችንን፣ ስዕለታችንን፣ ምልጃችንን ሁሉ ተቀብሎ ይፈጽምልናል። ስለዚህም ነው በሀገራችን በኢትዮጵያ በልዩ ልዩ ታቦት ስም የፈለቀው ፀበል ህመምተኞችን የሚፈውሰው። ታዲያ ይህ እንዲህ ያለው ፈውስ የሚገኘው በእውነት ለሚያምኑ ብቻ ነው። ለማያምኑ አይሰራም።

ጽላት ያለን እኛ ኢትዮጵያውያን ብቻ ነን። ሌሎች ክርስቲያኖች የላቸውም። ምክንያቱም እኛ ጽላትን የተቀበልነው ከብሉይ ኪዳን ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት ለ1ሺ አመታት የብሉይ ኪዳንን እምነት ተቀብለን እንደ እብራውያን አንድ አምላክ ብለን እናምን እናመልክ ነበር። ለዚህም ማስረጃ ኢትዮጵያውያን በየአመቱ ወደ ኢየሩሳሌም እየሄዱ ይሰግዱ ነበር።

የንግሥት ህንደኬ ባለሟል ከዚያ ሰግዶ ሲመለስ ነው በፊሊጶስ የተጠመቀው። (የሃ ስራ 8፡26-40) ከዚህ ወዲያ ነው እኛ ክርስትናን ተቀብለን ያለምንም ችግር ለመኖር የቻልነው። ሌሎች ግን፤ አሕዛብ ስለነበሩ ከክርስቶስ ወዲህ ስለሆነ ያመኑት፣ የተጠመቁት ጽላት የላቸውም። በተለይም መናፍቃን ጽላት በብሉይ ኪዳን ጊዜ ነብር፤ አሁን በሃዲስ ኪዳን ጊዜ ቀርቷል እያሉ እንደሚያወናብዱ የታወቁ ናቸው። ነገር ግን እራሱ ጌታችን ያለውን፣ እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። (ማቴዎስ 5፡17-19) የሚለውን ማስረጃ መስጠቱ በቂ ነው። በሉቃስ 16፡17 "ነገር ግን ከሕግ አንዲት ነጥብ ከምትወድቅ ሰማይና ምድር ሊያልፍ ይቀላል።" ሲል የተናገረውን እናገኛለን። የራስን እምነት ጠንቅቆ አውቆ መያዙ ያስከብራል፣ ፀጋን በረከትም ይሰጣል።

እንግዲህ ታቦት ማለት የእግዚአብሔር ማደርያ ማለት ነው ብለናል። በሌላ አነጋገር ደግሞ በክርስቶስ አምነው የተጠመቁ ክርስቲያኖችም የእግዚአብሔር ማደርያዎች፣ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሶች ተብለው ይጠራሉ። ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ እናንተ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ። (1 ቆሮንቶስ 3፡16-17) በማለት ቅድስናችንን ንጽህናችንን፣ ሃይማኖታችንን ጠብቀን እንድንኖር ያስተምረናል። ይህንንም ለማድረግ እግዚአብሔር ይርዳን።

ታሪኩን እንደተማርነው ታቦተ ጽዮን ዳጎን የተባለውን የኤሎፍላያንን ጣኦት ሰባብራ እንደጣለችው፣ ያደረገችውን ታላቅ ታምር ተመልክተናል። የኛም ሰውነት በታቦት ተመስሏል። ስለዚህ በታቦት የተመሰለው ሰውነታችን የእግዚአብሔር መንፈስ የአደረበት በመሆኑ ሰይጣን ድል ሊያደርገው አይችልም። ሰይጣንን አሸንፎ የማባረር ኃይል አለውና። ነገር ግን ሰውነታችን ለሰይጣን ሊሸነፍ የሚችለው የእግዚብሔርን ሕግና ትእዛዝ እንደ ኤሊ ልጆች አፍርሰን የማይገባ ስራ የሰራን እንደሆነ ነው። ስለዚህ

የማያስቀይም ሥራ ሰርተን የሰይጣን ተገዢዎች፣ አሽከሮች ከመሆን አምላካችን ይርዳን። የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን። ሁላችንንም ለንስሃ ሞት ያብቃን።

አሜን።